# የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እና ኢሕአዴግ፤ ከዚኽ ወዴት?

*ከአያል ሰው ደሴ፦ የግል አስተያየት*
***ክፍል አምስት*** *(ከክፍል አራት የቀጠለ)*

## ሐ - ፩፡- የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ)፤

በአገራችን የተደራጀ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ታሪክ የተለያዩ ፖለቲካዊ አመለካከቶችና ፍልሥፍናዎችን የሚከተሉ፣ አልፎም ተፃራሪ አስተሳሰቦችን የያዙና በተመሣሣይ የፖለቲካ ቅኝት ውስጥም ሆነው ነፍስ እስከ-መጠፋፋት በደረሰ ሁኔታ በምር ጠላትነት የተፈራረጁ የፖለቲካ ድርጅቶችን በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ከማስቀመጥ አልፎ በጋራ ለመታገል ቆርጠው የጋራቸው የሆነ ድርጅት መሥርተው በአንድነት የታገሉበት የመጀመሪያው የጋራ የትግል መድረክ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ) ነው፡፡

ምንም እንኳን ወቅቱ 'ቀዝቃዛው ጦርነት' የተባለው ዓለምን በአብዛኛው በሁለት አስተሳሰቦች ከፍሎ ያወዛወዘ ሥሪት በሶቭየት ኅብረት ሥር የነበረው የምሥራቁ ክፍል እራሱን መሸከም አቅቶት መፈረካከስ የጀመረበት ወቅት ቢሆንም፣ ደርግን ከወዳቂው ክፍል ወግኖ ያየው የምዕራብ ክፍል የመንግሥቱ ኃይለ-ማርያምን አገዛዝ ለማስወገድ የነበረውን የቆየ ጥረት ከማፋፋም ወደ-ኋላ አላለም፡፡ ደርግም በምሥራቅ ደጋፊዎቹ የውስጥ ማሽቆልቆል ምክንያት የሚያገኘው እርዳታ መቀነስ በአገሪቱ ውስጥ ከጦር-ሜዳ እስከ ከተማው እያደገና እየከፋ ከመጣው ዙሪያ-ጥምጥም ውጥረት ጋር ተዳምሮ በደረሰበት ጫና ተገድዶ እየተናነቀውም ቢሆን በጣም ከመሸ በኋላ አንዳንድ መሻሻሎችን ለማድረግ መሞከሩ አልቀረም፡፡ አገራችንም በአንድ በኩል ፀረ-አንድነት ኃይሎች ከምዕራቡ ኃያላንና ከሌሎች በተለይም ከአጎራባች አገር ሱዳን እንዲሁም የዐረብ አገሮች የሚያገኙት ሁል-አቀፍ እርዳታ በአደባባይ የወጣበት፣ በአኳያው የደርግ መንግሥት አይቀሬው መንኮታኮቱ ይበልጥ ግልጥ እየሆነና በፍጥነት እያሽቆለቆለ የሄደበትና በተለይ ሸዓብያና ሕወሓት ይበልጥ እየጎለበቱና የቁጥጥራቸውን አድማስ እያሰፉ፣ ሚዛኑ ወደ-እነሱ እያደላና ሁኔታው መቀልበስ አስቸጋሪ ወደ-ሆነበት ደረጃ እያደገ የመጣበት፣ ሕዝብም ቀጣዩ ምን እንደሚሆን እርግጠኛ ያልሆነበትና ተስፋው የጨገገበት፣ በሌላ በኩል የአንድነት ኃይሎች ያልተሰባሰቡበትና አንፃራዊ ከባድ ድክመት ላይ የነበሩበት ሁኔታ የተንፀባረቀበት ወቅት ነበር፡፡

ይኽ የማያስተማምንና ሕዝብን ወደ-አልተረጋገጠ ዋዥቂ ሁኔታ ሊያመራ፣ አገርንም ሊበትን የሚችል አሳሳቢ ሁኔታ እረፍት የነሣቸው ድርጅቶችም ሆኑ አገር-ወዳድ ግለሰቦች ደርግን ተቃውመው የቆሙ ሁሉ እንዲሰባሰቡና መላ-እንዲመቱ ጥረት አደረጉ፡፡ በመሆኑም ቀደም-ሲል እንደተጠቀሰው በምር ጠላትነት ሲተያዩ የነበሩ የአንድነት ኃይሎች ሳይቀር ያለፈ ቁርሾአቸውን ወደ-ኋላ በማድረግ እንደ-አንዲት አገር ዜጎች የጋራ መፍትኄ ለመሻት ቆርጠው ተነሱ፡፡ ለዚኽም በድርጅት ያልታቀፉ አገር-ወዳድ ኢትዮጵያውያንን በመጨመር በሐምሌ ወር ፲፱፻፹፪ ዓ/ም (1990) በቶሮንቶ፣ ካናዳ ታላቅ ስብሰባ ተደረገ፡፡ በዚኽ ሁሉም ተገኝቶ እንዲሣተፍበት የታሰበ ስብሰባ ላይ ሸዓብያም ሕወሓትም እንዲገኙ ጥሪው ተላልፎ ጥረትም ተደርጎ ነበር፡፡ ስብሰባው የአገሪቱን አሳሳቢ ሁኔታ ገምግሞ ***"በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምን ለመፍጠርና ዴሞክራሲን ለማስፈን ሁሉም ኢትዮጵያውያን ኃይሎች የሚሣተፉበት ሠፊ ጉባዔ እንዲጠራ..."*** የሚል ውሳኔ በማስተላለፉ፣ ከዘጠኝ ወራት ዝግጅት በኋላ ለጥሪው በጎ ምላሽ የሰጡ ወገኖች ኒው ዊንዘር፣ ሜሪላንድ ውስጥ ታላቅ ጉባዔ በማድረግ ***"በግልም ሆነ በማኅበር የነበሩና ያሉ ልዩነቶችን አቻችሎ፣ የግልም ሆነ የቡድንን ጥቅምና ፍላጎት ለአገርና ለወገን ፍቅር ተገዥ በማድረግ፤..."*** አራት የፖለቲካ ድርጅቶችን (የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት - ኢዴኅ፣ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ - ኢሕአፓ፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራቲክ አንድነት -ኢዴሕአ፣ የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ - መኢሶን) እና ወደ አምሣ የሚጠጉ ልዩ ልዩ የሲቪክና የሙያ ስብስቦችና ታዋቂ ግለሰብ ተወካዮች ሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም (April 17, 1991) የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ

ኃይሎች ቅንጅትን (ኢ.ዴ.ኃ.ቅ) መሠረቱ፡፡ (ቆየት ብሎ የኢትዮጵያ ፌዴራል ዴሞክራቲክ ፓርቲና ሌሎች ድርጅቶች ኢ.ዴ.ኃ.ቅን ተቀላቅለዋል)፡፡ ዋነኛ ዓላማውም በአገራችን **"ለሰላማዊ ሽግግር የሚያመች ሁኔታን ለመፍጠር ያልተቆጠቡ ጥረቶችን ማድረግ፤..."** እንደሆነና **"... ለዚኽም ከሌሎች ተቃዋሚ ኃይሎች ሆነ ከመንግሥት ጋር ... ውይይት ማድረግ..."** እንደሆነ ግልፅ ተደረገ፡፡ በዚኽም መንፈስ ኢ.ዴ.ኃ.ቅ ሕዝብን ከትርምስና አገርን ከብተና ለመታደግ ከሕወሓትም ሆነ ከሸዓብያ እንዲሁም አክራሪውን አመራር ባስወገደ መልክ ከደርግም ጭምር ሁሉን-አቀፍ የሆነ የጋራ የሽግግር መንግሥት ማቋቋምን እንደ ዓላማ ይዞ በመነሣት ለተግባራዊነቱ ጥረት አድርጓል፡፡ ይሁንንናም ለዚኽ በጎ ጥረት ጆሮ ያልሰጡ ሸዓብያና ሕወሓት የራሳቸውን የተቀናበረ ዘመቻ ከአጋሮቻቸው ጋር ጎን-ለጎን ማስኬዳቸውን ከማፋጠን ወደ-ኋላ አላሉም፡፡ በዚኽ ጊዜ ከሞላ ጎደል የኃይል አሠላለፉ በአንድ በኩል ኢ.ዴ.ኃ.ቅ፣ ከኢ.ሕ.ዴ.ን ጋር "ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ" የሚል አዲስ ቀሚስ የለበሰው ሕወሓትና አጋሩ ሸዓብያና ተባባሪው ኦነግ፣ በሌላ በኩል የሁሉም እርብርብ የሚደረግበትና በመፈረካከስ ላይ ያለው ደርግ ነበር፡፡

ኢ.ዴ.ኃ.ቅ ደርግ ገና እየተንገዳገደ ባለበት ጊዜ ከመውደቁ በፊት በአገሪቱ ለውጥ እንዲመጣ የሚሹ ኃይሎች ሁሉ ተባብረው የጋራ የሽግግር መንግሥት ለማቋቋም የተመሠረተ ቢሆንም ሁኔታዎች እየቀደሙ፣ ስመ-ክፉውና ተግባረ-ብልሹው የለንደን ጉባዔ ሁሉን-አቀፍና ትርጉም ያለው እንዲሆንና አገርን እንዳይበትን ከመታገል ጀምሮ የአዲስ አበባው "የሰኔ ጉባዔ" አግላይ እንዳይሆንና እራሱን (ኢ.ዴ.ኃ.ቅን) ጨምሮ ኅብረ-ብሔራዊ ድርጅቶች እንዲሣተፉበት እንዲደረግ፣ ያ ጉባዔ ያቋቋመው "የሽግግር መንግሥትም" አንድ የሽግግር መንግሥት ማድረግ ከሚችለው ውጭ ብሔራዊ ተቋማትን የማፍረስም ሆነ አገሪቱንና ሕዝቧን በዘላቂነት በሚያናጉ ተግባራት ላይ እንዳይሠማራ፣ ሰሜናዊው የአገሪቱ ክፍል የሆነችው ኤርትራ ኢ-ፍትኃዊና ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ እንዳትገነጠል የራሱን ሕግና የትሥሥር ደንብ ለመጣስ ከተዘጋጀው የተባበሩት መንግሥታት፣ ከጀርባ ዋና ተዋናይ ከሆኑት የአሜሪካና የእንግዚዝ መንግሥታት፣ ወዘተ..፤ በተለይም በታሪክ ታይቶም ተሰምቶም በማይታወቅ እጅግ አሣፋሪ ሁኔታ አገሬን ካልገነጠላችሁልኝ ብሎ በደብዳቤ ሣይቀር ሽንጡን ገትሮ ሙግት ከገጠመ የአቶ መለስ "የሽግግር" የሽንሽና መንግሥት ጋር ሙሉ ኃይሉን አንቀሳቅሶ ታግሏል፡፡ የደርግ አስከፊ ሥርዓት ከተውሸለሸለ አመራሩ ጋር መወገዱ፣ ለዚኽም በተለይ የምዕራቡ ዓለም ለተተኪዎቹ የሰጠው ጭፍንና ደፈናዊ ድጋፍ፣ እነ ሕወሓት ከተከተሉት ቋንቋንና ጎሣን መሠረት ካደረገ አዲስ የተጧጧፈ መሰሪያዊ የፖለቲካ አቅጣጫ ጋር ተደማምሮ ያሳደረው ጫና በአገር ውስጥ ይሁን ከአገር ውጭ በነበረው ኢትዮጵያዊ ኅብረተሰብ ውስጥ ብዙ ወገኖች ሁኔታው በአጠቃላይና አዲሶቹ ገዥዎች የያዙት ፍልሥፍናም ሆነ አጠቃላይ ቅኝት በአገሪቱ ላይ የሚያስከትለውን አደጋ በቅጡ ለማብላላትና ለማሰላሰል እንዳይችሉ ብዥታን የፈጠረባቸው ይመስለኛል፡፡ በመሆኑም አጠቃላይ ሁኔታው ኢ.ዴ.ኃ.ቅ ለነበሩ ክስተቶችና ምላሽ መስጠት የተገደደበትና በሱም ላይ ተጠምዶ ከመነሻው በያዘው አደረጃጀትና አሠላለፍ ተቆልፎ በተከላካይነት ላይ ያተኮረ ቅኝት በቀጣይነት መያዙ አይቀሬ እጣው ነበር፡፡

ኢ.ዴ.ኃ.ቅ ሁሉን-አቀፍና ማንንም ያላገለለ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም ያደረገው ትግል ውጤት አስቀድሞ በተዘጋጀ አግላይና ኢ-ዴሞክራሲያዊ የትዕቢት መንገድ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ እራሱን በሽግግር ስም ከሰየመ ጀምሮ የአገሪቱ የዴሞክራሲ ሂደት በአዲስ መልክ እንዲቃኝ ጥረቱን አላቋረጠም፡፡ በመሆኑም ከኢ.ዴ.ኃ.ቅ ውጭ ያሉ ኃይሎችን በጨመረና ማንንም ባላገለለ ሁኔታ አጠቃላይና አገር-አቀፍ ጉባዔ ተደርጎ ከአጀማመሩ ፈር የለቀቀውንና እየቆየም በግልፅ አቅጣጫውን እየሳተ የነበረውን የሽግግር ሂደት በአዲስ መልክ አገር-አቀፍ የእርቅና የሰላም ሂደትን በመከተል አቅጣጫው እንዲስተካከል ሞክሯል፡፡ በዚያም መንፈስ በመጋቢት ወር ፲፱፻፹፭ ዓ/ም (1993) በፓሪስ ከተማ 'ፓሪስ-አንድ' በመባል የታወቀውን፣ "የሰላምና እርቅ ኮንፈረንስ በኢትዮጵያ"፣ በመቀጠልም ከታኅሣስ ፱-፲፫ ፲፱፻፹፮ (1994) በአዲስ አበባ ከተማ የተካሄደውና የኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤትን የመሠረተው "ሰላምና እርቅ በኢትዮጵያ አገር-አቀፍ ጉባዔ"፣ ከዚያም በ ፲፱፻፺ ዓ/ም (1997) "ፓሪስ-ሁለት" በመባል የሚታወቀውንና የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ኅብረት (ኢ.ተ.ፖ.ድ.ኅ) የተሰኘውን የጋራ የትግል

መድረክ የፈጠረው ስብሰባ፣ ወዘተ... እውን እንዲሆኑ ከጅምሩ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። ያለ ኢዴኃቅ ያላሰለሰ ጥረትና ግንባር-ቀደም ሚና እነዚኽ ጉባዔዎች እውን ሊሆኑ እንደማይችሉ ግልፅ ነው።

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ኢሕአዴግ ሥልጣን ከመያዙ በፊትም ሆነ ለሥልጣን ከበቃ በኋላ ኢዴኃቅ እንዲመሠረቱ ጥረት ባደረገባቸው ስብሰባዎች ላይ ሁሉ እንዲገኝና ተሣታፊ እንዲሆንም ሆነ ጉባዔዎቹ ባስተላለፏቸው ውሳኔዎች መሠረት ኢሕአዴግ ሁሉን-አቀፍ በሆነ መንገድ ትክክለኛ ብሔራዊ እርቅና ሰላም ላይ የተመሠረተ ዘላቂ ሰላም በአገራችን እንዲኖርና ሕዝባችን መብቶቹን የሚያስከብርበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት እንዲሆን የዴሞክራሲ ሂደቱ ፈር እንዲይዝ ፍላጎቱንና ቁርጠኝነቱን በመግለፅ ጥሪውን በደብዳቤዎች ሳይታክት አስተላልፏል። በእብሪት የተወጠሩት የኢሕአዴግ መሪዎች ግን እንኳን መንግሥታዊ ኃላፊነት እንደያዘ ክፍል ከማንም ስለ ሰላምና ሥነ-ሥርዓት መጠነኛ ትውውቅ ካለው ተራ ሰው የሚጠበቀውን ያኽል ድፍረትና ሥነ-ምግባር አጥተው ለአንዳቸውም መልስ አለመስጠት ብቻ ሣይሆን ደብዳቤዎች እንደደረሷቸው እንኳን እውቅና መስጠት አልሞከሩም። ያም ሆኖ ኢዴኃቅ ጥር ሰላሣና መጋቢት አንድ ፲፺ ዓ/ም በአሜሪካ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ኮንግረስ) የአፍሪቃ ጉዳይ ንዑስ ኮሚቴ የወቅቱ ሰብሳቢ በነበሩት የተከበሩ አቶ ሃሪ ጆንስተን አነሳሽነት የኢሕአዴግ የሽግግር መንግሥትንና ተቃዋሚ ክፍሎችን ለማነጋገር በተደረገው ስብሰባም ሆነ በፕሬዝደንት ክሊንተን አስተዳደር ብሔራዊ የፀጥታ ክፍል አማካይነት በዋይት ሐውስ በተደረገው ስብሰባ እንዲሁም በቀድሞው ፕሬዝደንት ጂሚ ካርተር አነሳሽነት አትላንታ በካርተር ማዕከል በተደረገው ውይይት ላይ ሳያቅማማ በመገኘት በአገራችን በኢትዮጵያ ከመስመር የወጣው የዴሞክራሲ ሂደት ቅጥ እንዲኖረው፣ የአገር አንድነት እንዳይናጋና የሕዝብ መብቶች እንዲከበሩ አማራጭ አሳቦችን በማቅረብ ታሪካዊ ድርሻውን ለመወጣት ጥሯል።

ኢዴኃቅ እነዚያን ጥረቶች በማድረጉና የአንድነት ትግሉ እንዳይከስም በማድረጉ በተለይ ጎሣን/ቋንቋን መሠረት ያደረገው የኢሕአዴግ የፖለቲካ ፍልሥፍናና ብሔራዊ ኃላፊነት በእጁ የጎደላቸው መርኃ-እቅዶቹ (ፖሊሲዎቹ) በተለይ በአገሪቱ አንድነት ላይና በሕዝባችን ትስስር ላይ ሊያደርሱ ከሚችሉት የባሰ ጉድ እንዲታቀብ ወይም በዚያ የክፍፍል ጎዳና መሄድ ብቸኛ መንገድ ሆኖ በዜጎች እንዳይወሰድ፣ በዚያ ጎሠኝነት ባበበበትና ዘይቤ ተደርጎ በተወሰደበት ወቅት ኢትዮጵያውያን በአንድነት ላይ የቆመ ልዩነቶቻቸውን አቻችለው ብቻ ሣይሆን በደስታ ተቀብለውና ተንከባክበው ሊኖሩ እንደሚችሉና እንደሚገባ እንዲሁም በጋራ ትግላቸው ሁሉም አትራፊና ተጠቃሚ ለሚሆንበት የተሻለ ሥርዓት ባለቤት ሊሆኑ እንደሚችሉና ጎሣን/ቋንቋን መሠረት ያደረገ ኋላ-ቀር መንግሥታዊ አወቃቀር አደገኛ ከፋፋይ እንደሆነ በማስረዳት የአንድነት መቅረዝ ያዥና አማራጭ ሆኖ ተገኝቷል።

ሆኖም እየተለወጠ የመጣው የአገሪቱ ሁኔታና ዓለም-አቀፍ ድጋፍን በሁሉም ረገድ በገፍ ማጋበስ ያልገደደው ኢሕአዴግ፣ በኢዴኃቅም ሆነ በሌሎች ወገኖችና በሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚቀርቡትን ውትወታዎች፣ ተማፅኖዎችና ጥያቄዎች ከቁብ አልቆጠረም። ኢዴኃቅ በአጠቃላይና በውስጡ ያቀፋቸው ድርጅቶች በተናጠል የአገር-ወዳድነት መንፈስም ይሁን ቁርጠኝነቱ፣ ልምዱም ሆነ የተሻለ ራዕይ መያዙ ሣይገዳቸው፣ ሕዝብ የሰጠው አመኔታ፣ የለገሰው በጎ-ፈቃድና ያልነፈገው መሰል-የለሽ ትብብር ሳይጓደል በመሠረታዊ ችግሮች ጥንውት ምክንያት የታሰበውን ውጤት ማስገኘት አልቻለም። ለሰመመ ውድቀትም ተዳርጓል። ለውድቀቱ አስተዋፅዖ ካደረጉት ውስጥ የአደረጃጀትና የአወቃቀር፣ አሉታዊ ሁኔታዎች፣ የትግል ትልም (ስትራቴጂ) እና የአመራር ችግሮች ዋነኞቹ ነበሩ ማለት ይቻላል። እያንዳንዳቸውን በአጭር በአጭሩ እንይ።

*1. አደረጃጀትና አወቃቀር፦* ቀደም ሲል እንደተገለፀው ኢዴኃቅ የብዙ ድርጅቶች፣ ስብስቦችና ግለሰቦች የጋራ የትግል መድረክ ነበር። በመሆኑም ከሞላ-ጎደል ከሥራ-አስፈፃሚ ኮሚቴ ጀምሮ ባሉ የድርጅቱ መዋቅራዊ ጠገጎች እነኝኽ ሁሉ ይወከላሉ። ይኽ ዓይነት አወቃቀር በተደላደለ የፖለቲካ ሁኔታና ግልፅ አሠራርን በሚጠይቅ የኅብረተሰብ ሥሪት ውስጥ አንዳንድ መሻሻሎችን ለማስገኘት ለሚደረግ ሕዝባዊ ትግል (ያውም የሲቪክና የሙያ

ማኅበራት የተፈተኑ፣ ተቀባይነት፣ ሕጋዊ ውክልናና ልምድ ባላቸው መሪዎች የሚመሩ፣ የሚያንቀሳቅሱት የሚታይ ኃይልና አስተማማኝ ተከታይ ያልቸው ከሆነ) ሊጠቅም ይችላል። የኢዴኃቅ ዓይነት አደረጃጀት ግን እንደ ኢሕአዴግ ዓይነትን ድርጅትና የሰፈነውን ከፋፋይ ሥሪት ለመታገል የሚጠይቀውን በውስጡ ሙሉ መተማመን ያለውና ወጥ የሆነ የጠበቀ ትስስር ያለው አመራር መኖርን፣ ምሥጢራዊነት የሚጠበቅበትና ውሳኔዎችን በቅልጥፍና ለማስተላለፍና ጠንከር ያሉ የውስጥ ለውጦችን ለማድረግ የሚስያችልም ሆነ የሚፈቅድ አወቃቀር አልነበረም። በተጨማሪም በተለይ በሲቪክም ሆነ በሙያ ዘርፍ ተደራጅተዋል የተባሉት ክፍሎች አብዛኞቹ ለተጠያቂነት የማያመቹ፣ ቀደም-ያለ ጎልውና ያልነበራቸውና በስም ብቻ የነበሩ በመሆናቸው ተሣትፏቸው እስከዚኽም እርባና ያለው አልነበረም። በአጠቃላይ የኢዴኃቅ አደረጃጀትና አወቃቀር በአሉታዊነት እየተለወጠ ለነበረው ሁኔታና ጠንካራ ማዕከልና ወጥ አደረጃጀትን ለጠየቀ ትግል መጣኝ አልነበረም።

*2. አሉታዊ ሁኔታዎች፤-* በአንድ በኩል ድኅረ-ቀዝቃዛው ጦርነት ያለው ዓለም በአንድ ልዕለ-ኃያል ማዕከልነት ሠልፉን እያስተካከለ የነበረበት ጊዜ ስለነበርና የዚኽ አንድ ዘርፍ ሥሪት ዋነኛ ክፍልና አብሮ ተሠላፊዎች በኢትዮጵያ የተደረገውን ለውጥ ከጥንስሱ የደገፉ ነበሩ። እነዚኽ ኃያላንና የበለፀጉ አገሮች አዲሶቹን የኢትዮጵያ/ኤርትራ ገዥዎች ከቆሙበት ፍልሥፍናም ሆነ ከሚከተሉት ምግባር ሣይሆን ደርግን ለማስወገድ ከነበራቸው ሚና አንፃር እና የኢትዮጵያ ሕዝብ የታገለውና አይከፍሉ መስዋዕትነት የከፈለው ከደርግ የተሻለ ሥርዓት ለማግኘት እንዳልነበር ሁሉ እነዚኽ አዲስ ገዢ ኃይሎች የሚወስዷቸውን ማንኛውንም ዓይነት እርምጃዎች ከደርግ ይዞታና ባኅሪ ጋር በማነፃፀር እያዩ እንዳላዩ መሆንን የመረጡበት፣ አልፎም የጠየቁትን ሁሉ ከማድረግ ወደ-ኋላ ያላሉበት ወቅት ስለነበር ለአንድነት ኃይሉ ድጋፍ ቀርቶ የሚያቀርበውን ክርክር በተገቢ ለማስተባቃትና ወደ-ኋላ እየቆዩ የተገነዘቡትን ትክክለኛ ገፅታ ለመረዳት ያልቻሉበት ወቅት ስለነበር፤ የኢዴኃቅ ጥረት የታሰበውን ያኽል ውጤት አላስገኘም። በሌላ በኩል አገዛዙ በተከተለው ሕዝብን ከፋፋይ መሰሪያዊ ጎሠኛ ፍልሥፍና ምክንያት በቅንጅቱ ውስጥ ከነበሩት ሣይቀር ልዩነት የታየበትና የመሰባሰብና የአደረጃጀት ዘይቤው ያንኑ ኋላ-ቀር ጎጠኛ መሥመር የመከተልና የማንፀባረቅ ጥንውት ያየለበት አሳዛኝም አሣፋሪም ጊዜ ስለነበር፣ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ የሚደረገው የአገር-ወዳዱ፣ ሕዝባዊና የአንድነት ኃይሉ ትግል ከፍተኛ እንቅፋትና ፈተና ገጥሞታል። ያ ሁኔታም እንደ አገር-አቀፍ ስብስብ ኢዴኃቅንም ጎድቶታል።

እንዲሁም ኢዴኃቅ በቀናዒ አገር-ወዳድነት መንፈስና ለኢትዮጵያ ሕዝብ እኩልነትንና ፍትኅን የሚያስገኝ ሥርዓት ለማስገኘት የጠና ፍላጎትና ቁርጠኝነት ያልቸው ከኢሕአፓ እስከ ኢሠፓ ያሉ ኃይሎችን ያቀፈ ስብስብ በመሆኑ በውስጡ የአመለካከትም ይሁን የአስተሳሰብ ልዩነቶች መከሰታቸው አዲስ ሊሆን አይችልም። በመለስተኛ መርኃ-ግብር (ፕሮግራም) ብቻ የተገናኙና ለተወሰነ ዓላማ በአቻነት አብረው የሚሠሩ ልዩ ልዩ የፖለቲካ ፍልሥፍናዎችን የሚከተሉ ድርጅቶችን ያቀፈ እንጂ የተዋኀደና አንድ ወጥ አደረጃጀት፣ አወቃቀርና አመራር ያለው ድርጅት ባለመሆኑም የአስስተሳሰብም ሆነ የአሰራር ልዩነቶች መከሰታቸው ሊጠበቅ የሚችል ጉዳይ ነው። ሆኖም በተለይ ትግሉን መስመር ለማስያዝ የግድ በሚልበት ፈታኝ ወቅት ላይ የተወሰነው ክፍል ከቅንጅቱ ተነጥሎ "መድኅን" በሚል አዲስ ድርጅት መቋቋሙ የጋራ ትግሉን በማያገግምበት ሁኔታ በእጅጉ ጎድቷል።

በተጨማሪም ……

***በክፍል ስድስት ይቀጥላል…..***